በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትሕ ቢሮ
የሕግ ምክር፣ማ ርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION DIRECTORATE

ቁጥር፡- የሕ/ምክ/ማር/ማጠ/......../18

ቀን ..../04/2018 ዓ/ም

## ለአብክመ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን

ባህርዳር

**ጉዳዩ፡-** የመመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/2017 አንቀጽ 16(4) መሰረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አስመልክቶ አዋጁ በወጣ በአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮ በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

ተቋማችሁ በአዋጁ መሰረት በቁጥር ት/ሎ/ባ/03/-360/18 በቀን 24/03/18 ዓ/ም በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 19/2016ን የላካችሁልን መሆኑ ይታወቃል፡፡

በእኛም በኩል የተላከልንን ይህን መመሪያ በአዋጁ መሰረት ተመልክተን መመሪያ ቁጥር 19/2016 ተብሎ ይጠራ የነበረውን በመመዝገብ በአዲስ **መመሪያ ቁጥር 34/2018 ዓ/ም** በሚል ሰጥተን የላክንላችሁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

መስፍን መኮንን

የሕግ ምክር፣ ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት
የክልል ዐቃቤ ሕግ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤(ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት
  ፍትህ ቢሮ

# መመሪያ ቁጥር 34/2018 ዓ/ም

# በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ባለስልጣን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማሻሻያ መመሪያ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 199/2014 አንቀፅ 7 ንኡስ አንቀጽ 42 በአሽከርካሪ፣ በተሽከርካሪ፣ በትራንስፖረት ልማት፣ በስምሪት፣ በመንገድ ደህንነት፣ በትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን እና በሎጅስቲክስ የስራ ክፍሎች ከሚሰጡ የአገልግሎቶች ክፍያ እና የቅጣት ገቢዎችን ይሰበስባል፣ የውስጥ ገቢ መመሪያ አዘጋጅቶ ይህንኑ ጥቅም ላይ ያውላል በሚል የተቀመጠ በመሆኑ፤

ባለስልጣኑ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን የአገልግሎት ክፍያ በግልፅ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

በተለያዩ መመሪያዎች ይሰበሰብ የነበረው የአገልግሎት ክፍያ ግልፅነት ባለው፣ በተደራጀ እና በተቀናጀ መንገድ በተዘጋጀ መመሪያ መከፈል ስላለበት፤

ከዚህ በፊት ክፍያ የማይፈፀምባቸው አገልግሎቶች ክፍያ እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፤

ከወቅታዊ ሁኔታው ጋር የተገናዘበ የአገልግሎት ክፍያዎችን አጥንቶ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የክልላችን የአገልግሎት ክፍያ ከሌሎች ክልሎች የአገልግሎት ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ስላለበት፤

ገቢ የመሰብሰብ አቅምን በማሳደግ በዘርፉ አገልሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማሟላት እና የመሰረተ ልማት ስራዎችን ማከናዎን የሚገባ በመሆኑ፤

ባለስልጣኑ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2014 በአንቀፅ 7 ንኡስ አንቀጽ 42 እና አንቀፅ 18 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የአገልግሎት ክፍያ ማሻሻያ መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 34/2018 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

በደንቡ እና በመመሪያ ቁጥር 33/2018 ትርጓሜ የተሰጣቸዉ ቃላት እንደ አግባቡ በዚህ መመሪያ ተፈጻሚ መሆናቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ **"ደንብ"** ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2014 ነው፤

2/ **"ባለስልጣን"** ማለት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ነው፤

3/ **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት ተቋሙ ለሚሰጣቸዉ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚያስከፍላቸው ክፍያ ማለት ነው፤

4/ **"ከአገልግሎት የሚገኝ ገቢ"** ማለት በባለስልጣኑ ስር በተደራጁ ዳሬክቶሬቶች እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ባሉ የዞን እና በሪጅኦ ፖሊታንት ከተማ ትራንስፖርት ተ/ጽ/ቤቶች ስር ያሉት በአሽከርካሪ፣ በተሽከርካሪ፣ በትራንስፖርት ልማት፣ በትራንስፖርት ስምሪት፣ በመንገድ ደህንነት፣ እና በትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን ብቃት ማረጋገጫ ቡድኖች ከሚሰጡት አገልግሎቶች የሚሰበሰብ የዉስጥ ገቢ ነው፤

5/ **"የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ"** ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን ለማሽከርከር የሚያስችል በፌደራል ደረጃ በወጣው በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 እና ከዚያ በፊት በወጡ ህጎች መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ነው፤

6/ **"የትራንስፖርት አገልግሎት ልማት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን፣ የመንገድ ደህንነት፣ የትራንስፖርት ስምሪት፣ የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ በጀት"** ማለት በባለስልጣኑ እና የተዋረድ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ግብዓቶችን ለማሟላት፣ የትራፊክ ኮምፕሌክስን በአግባቡ ለማደራጀት፣ በስራ ላይ የሚያጋጥሙ ብልሽቶችን በወቅቱ አስጠግኖ ያልተቆራረጠ አገልግሎት ለመስጠት፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ሊያዘምኑ የሚችሉ ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን እና አሰራሮችን ለማልማት እና ለሌሎች ለዚሁ ስራ አገልግሎት ማሚያ የሚውል የውስጥ ገቢ በጀት ማለት ነው፤

7/ **"የተሽከርካሪ ድንገተኛ ቴክኒክ ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ አገልግሎት ሲሰጥ የቴክኒክ አቋሙ የተሟላ መሆኑን በባለሙያዎች ድንገተኛ ምርመራ ተደርጎለት በምርመራ ወቅት የተገኙ ጉድለቶችን አስተካክሎ ሲመጣ የሚከፈለው ክፍያ ነው፤

8/ **"የተሽከርካሪ ድንገተኛ ቴክኒክ ምርመራ የአገልግሎት ቅጣት ክፍያ"** ማለት ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ በድንገተኛ ቴክኒክ ምርመራ ወቅት የተገኘበትን ጉድለት እንዲያስተካክል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስተካክሎ ካልመጣ ከመደበኛ የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት ክፍያ ተጨምሮ የሚከፈል ነው። አገልግሎት ሲሰጥ የቴክኒክ አቋሙ የተሟላ መሆኑን በባለሙያዎች ምርመራ ተደርጎለት በምመራ ወቅት የተገኙ ጉድለቶችን አስተካክሎ ሲመጣ የሚከፈለው ክፍያ ነው፤

9/ **"የኮምፒዩተር ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ"** ማለት ማንኛውም የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት፣ ለማሳደስ፣ የእድሳት ጊዜያቸው ላለፈባቸው በቅጣት የሚሰበሰብ ክፍያ፣ ቅጅ ወይም የትክ አገልግሎት ሲሰጥ ለሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ነው፤

10/ **"የምርመራ ሰርተፊኬት"** ማለት ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አድርጎ የቴክኒክ ብቃቱን ላሟላ ተሽከርካሪ የሚሰጥ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ነው፤

11/ **"ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት (ቦሎ)"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥና ለአንድ ዓመት የሚፀና ተለጣፊ ምልክት ነው፤

12/ **"ቀረጥ"** ማለት በትክክል ለእቃው በተደረገ ጠቅላላ ወጭ ላይ ተመስርቶ እና የዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሠረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ታሪፍ ነው፤

13/ **"የቴምብር ቀረጥ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 110/1990 መሠረት ማንኛውም ሰው ንብረት በስሙ ሲያስመዘግብ በስሙ በሚያስመዘግበው የንብረት መጠን ተሰልቶ የንብረቱን መጠን 2% ለመንግስት እንዲከፍል ማድረግ ማለት ነው፤

14/ **"ልዩ ተንቀሳቃሽ"** ማለት ሰው ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተንቀሳቃሽ ሳይሆን ለእርሻ፤ ለአትክልት፣ ለከብት፣ ለመንገድ፣ ለህንፃ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማንኛውም ተመሳሳይ ስራ የተሰራ ወይም ለዚህ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

15/ **"ስም ማዛወር"** ማለት በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመሳሰሉት ምክንያቶች በተሽከርካሪ ላይ የሚከናወን የባለቤትነት ይዞታ ለውጥን የሚያጠቃልል ነው፤

16/ "የምዝገባ አገልግሎት ለውጥ" ማለት ተሽከርካሪው ከሚሰጠው አገልግሎት ወደ ሌላ አገልግሎት ዘርፍ ሲቀየርና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሠሌዳ ኮድ በመለወጥ የሚከናወን ነው፤

17/ **"የምዝገባ ስረዛ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ ተመዝግቦ ሲሰራበት ከነበረው አገልግሎት በእርጅና፣ በአደጋ፣ በመለዋወጫ (spare parts) እጥረት ተሽከርካሪው ከአገልግሎት ውጭ በመሆኑ ሠሌዳና ሊብሬ ሲመልስ የሚከናወን ስረዛ ማለት ነው፤

18/ **"አዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ"** ማለት ከዚህ በፊት በፌደራል ወይም በክልል ተራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ምዝገባ ያልተደረገላቸው አዲስም ሆነ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን አዲስ ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ ማለት ነው፤

19/ **"ቋሚ ሰሌዳ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ የሚያስፈልጉት ህጋዊ ሰነዶች ተሟልተውና ተገቢው ምርመራና ምዝገባ ከተደረገለት በኋላ ከተሽከርካሪው ከፊትና ከኋላ የሚለጠፍ በስራ (አገልግሎት) ዓይነት ተለይቶ የሚሰጥ ቋሚ የሰሌዳ ቁጥር ነው፤

20/ **"ከቀረጥ ነፃ"** ማለት በጉምሩክ ደንብ መሠረት በገቢና ወጭ እቃዎች ላይ ከሚጣልና ከሚሰበሰብ ቀረጥና ታክስ ነፃ መሆን ማለት ነው፤

21/ **"የሻንሲና የሞተር ቁጥር ምት ምዝገባ አገልግሎት"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በጉዳት እና በተለያየ ምክንያት የሞተር ቁጥር ወይም የሻንሲ ቁጥር በአዲስ ሲቀየር የቀድሞውን ቁጥር በመቀየር አዲሱን የመመዝገብ ተግባር ማለት ነው፤

22/ **"ሊብሬ"** ማለት የተሽከርካሪ መሠረታዊ ክፍሎች እና የባለንብረቱ ስም የተፃፈበት ተሽከርካሪው በህጋዊ መልኩ ምዝገባ ለማድረጉ እና ለባለንብረቱ የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ በዞንና በሪጅኦፖሊታን ከተሞች ትራንስፖርት ጽ/ቤቶች የሚሰጥ ደብተር ነው፤

23/ **"የስልጠና ምድብ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1074/2010 ላይ የማሽከርከር ብቃት የስልጠና ምድቦችን (አውቶ፣ ባለሶስት እግር፣ ህዝብ 1፣ ህዝብ 2፣ ህዝብ 3፣ ደረቅ 1፣ ደረቅ 2፣ ደረቅ 3፣ ፈሳሽ 1፣ ፈሳሽ 2 እና የልዩ ማሽነሪዎች የማሽከርከር የብቃት ማረጋገጫ ያጠቃልላል።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን እና በተዋረዱ በሚገኙ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ አገልግሎት ክፍያዎች

4. <u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ</u>

| ተ.ቁ | የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 1 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ) | 1500 |
| 2 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተበላሽቶ ትክ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ) | 1500 |
| 3 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጠፍቶ ትክ ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ) | 3000 |
| 4 | የደረጃ መንጃ ፈቃድ የእድሳት ጊዜው ከ2 ወደ 4 ዓመት በማራዘም ለአዲሱም ሆነ ለደረጃ ለሁሉም ምድቦች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት፤ | 1400 |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች | አዲሱ የአገልግ ሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 5 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ጊዜው ሲያልፍ (ለሁሉም ምድብ) ቅጣት | |
| 5.1 | እስከ አንድ ወር ድረስ | 300 |
| 5.2 | ከአንድ ወር በኂላ እስከ 3 ወር ድረስ | 800 |
| 5.3 | ከ3 ወር በኂላ እስከ አንድ አመት ድረስ | 1500 |
| 5.4. | ለመንጃ ፈቃዱ ለህትመት የሚከፈለው ብር 1500 እደተጠበቀ ሆኖ ሳይታደስ አንድ ዓመት ካለፈው ለንድፈ ሃሳብ እና ለተግባር ለፈተና እስከ 3 ዓመት | 2500 |
| 5.4.1 | ከ3 ዓመት በኂላ እስከ 5 ዓመት | 5000 |
| 5.4.2 | ከ5 በኂላ እስከ 10 አመት | 7500 |
| 5.4.3 | ከ10 ዓመት በኂላ መንጃ ፈቃዱ መክኖ በአዲስ ሰልጥኖ ማውጣጥ ይችላል፡፡ | |
| 6 | የመንግስት ተሿሚዎች የማሽከርካር ልዩ መንጃ ፈቃድ መስጠት | 400 |
| 7 | የመንግስት ተሿሚዎች ልዩ መንጃ ፈቃድ ለማሳደስ | 300 |
| 8 | የመንግስት ተሿሚዎች የማሽከርካር ልዩ መንጃ ፈቃድ የማደሻ ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት | |
| 8.1 | እስከ አንድ ወር ድረስ | 100 |
| 8.2 | ከአንድ ወር በኂላ እስከ 3 ወር ድረስ | 200 |
| 8.3 | ከ3 ወር በኂላ እስከ አንድ አመት ድረስ | 300 |
| 8.4 | ሳይታደስ አንድ ዓመት ካለፈው | 500 |
| 8.5 | የመንግስት ተሿሚዎች ልዩ መንጃ ፈቃድ ሲጠፋና ሲበላሽ ትክ ለመስጠት | 400 |
| 9 | መንጃ ፈቃድ ከመከላከያ ወደ ሲቪል ለመቀየር (ለሁሉም ምድቦች) | 1500 |
| 10 | የመንጃ ፈቃድ ፋይል ዝውውር (ለሁሉም ምድቦች ለመላክም ሆነ ለመቀበል) | |
| 10.1 | በክልሉ ውጥ ከዞን ዞን ከሆነ | 500 |
| 10.2 | ከክልል ክልል ከሆነ | 700 |
| 11 | ለአፕሮቫ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ መስጠት | 7000 |
| 12 | የአፕሮቫ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ለማደስ | 5000 |
| 13 | የአፕሮቫል ማሰልጠኛ ተቋም የፈቃድ እድሳት ጊዜው ካለፈ ቅጣት | |
| 13.1 | እስከ አንድ ወር ድረስ | 500 |
| 13.2 | ከአንድ ወር በኂላ እስከ 3 ወር ድረስ | 1000 |
| 13.3 | ከ3 ወር በኂላ ከ13.2 ካለው ቅጣት ላይ በየወሩ ብር 1000.00 እየተጨመረ ይከፈላል፡፡ | |
| 13.4 | አፕሮቫ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድዱ ሲጠፋ ወይም ሲበላሽ ትክ መስጠት | 1500 |
| 14 | የቴክኒሻን የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ (አፕሮቫል) ሲሰጥ (ለሁሉም ምድብ) | 800 |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 15 | አፐሮቫል ሰርትፍኬት ለማሳደስ (ለሁሉም ምድብ) በአንድ ሰርትፍኬት | 500 |
| 16 | የቴክኒሻን የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ (አፐሮቫል) ሲጠፋና ሲበላሽ ትክ መስጠት | 800 |
| 17 | አፐሮቫል ሰርትፍኬት የእድሳት ጊዜው ሲያልፍ (ለሁሉም ምድብ በአንድ ካርድ) ቅጣት | |
| 17.1 | እስከ አንድ ወር ድረስ | 300 |
| 17.2 | ከአንድ ወር በኋላ እስከ 3 ወር ድረስ | 500 |
| 17.3 | ከ3 ወር በኋላ እስከ አንድ አመት ድረስ | 1000 |
| 17.4 | ከአንድ አመት በኋላ እስከ 2 ዓመት | 2000 |
| 17.5 | ሳይታደስ 2 ዓመት ካለፈው የማሰልጠን ፈቃዱ ተሰርዞ በአዲስ ሰልጥኖ ማውጣት ይችላል | |
| 18 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሰራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት አዲስ ፈቃድ መስጠት | 8000 |
| 19 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የአድራሻ ለውጥ ሲያደርጉ | 5000 |
| 20 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ቅርንጫፍ ሲከፍቱ | 8000 |
| 21 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የተሽከርካሪ ለውጥ ሲያደርጉ | 500 |
| 22 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የማስፋፊያ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ለአንድ ተሽከርካሪ የአገልግሎት ክፍያ | 1000 |
| 23 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሰራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት ፈቃዳቸው ሲታደስ | 5000 |
| 24 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የፈቃድ እድሳት ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት | |
| 24.1 | እስከ አንድ ወር ድረስ | 1000 |
| 24.2 | ከአንድ ወር በኋላ እስከ 3 ወር ድረስ | 3000 |
| 24.3 | ከ3 ወር በኋላ እስከ 5 ወር | 5000 |
| 24.4 | ከ5 ወር በኋላ አንድ አመት እስኪሞላው ከብር 5000.00 ላይ በየወሩ ብር 1000.00 እየተጨመረ ይከፈላል፡፡ ፈቃዱን ሳያሳድስ አንድ ዓመት ካለፈው የማሰልጠን ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ | |
| 25 | የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም የራሳቸውን ሰራተኞች ለሚያሰለጥኑ ሌሎች ተቋማት ፈቃዱ ሲጠፋ ወይም ሲበላሽ ምትክ ሲሰጥ | 1500 |
| 26 | የልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲሰጥ | 8000 |
| 27 | የልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲታደስ | 5000 |
| 28 | የልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ የማደሻ ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት | |
| 28.1 | እስከ አንድ ወር ድረስ | 500 |
| 28.2 | ከአንድ ወር በኋላ እስከ 3 ወር ድረስ | 1000 |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ የአገልግሎት ዓይነቶች | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 28.3 | ከ3 ወር በኂላ ከ28.2 ካለው ቅጣት ላይ በየወሩ እየተደመረ የሚከፈል | 1000 |
| 29 | የልዩ ማሽነሪ ማሰልጠኛ ተቋም ፈቃድ ሲጠፋ እና ሲበላሽ ትክ ለመስጠት | 1500 |
| 30 | የሀገር ውስጥ መንጃ ፈቃድ ኢንተርናሽናል ደብዳቤ ለመፃፍ | |
| 30.1 | ለኢትዮጵያዊያንና ለትውለደ ኢትዮጵያዊያን መንጃ ፈቃዱን ስለ ትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ለሰጠው ዞን (ከተማ) ብር 500.00 ይከፍላል | 2500 ክልል |
| 30.2 | ለወጭ ዜጎች 500.00 ዞን ይከፈላል | 5000 ክልል ላይ |
| 31 | የውጭ መንጃ ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስቀየር | |
| 31.1 | ለኢትዮጵያዊያንና ለትውለደ ኢትዮጵያዊያን ክልል ላይ ብር 500.00 ይከፈላል | 1500 መንጃ ፈቃዱ ከሚቀየር በት |
| 31.2 | ለወጭ ዜጎች ክልል ላይ ብር 1000.00 ይከፈላል | 1500 መንጃ ፈቃዱ ከሚሰጥበት |
| 32 | የመደበኛ የአሽከርካሪ ብቃት ሰልጣኞች የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ፈተና ለመፈተን ቀጠሮ ለማሳዝ | 500 |
| 33 | ፈተና ለወደቁ ዳግም የተግባር እና የንድፈ ሃሳብ ለመፈተን ቀጠሮ ማሳዣ፣ | |
| 33.1 | ለመጀመሪ ዙር የድጋሜ ፈተና ቀጠሮ ለማሳዣ | 400 |
| 33.2 | ለሁለተኛ ዙር የድጋሜ ፈተና ቀጠሮ ለማሳዣ | 500 |
| 33.3 | ለሦስተኛ ዙር የድጋሜ ፈተና ቀጠሮ ማሳዣ (ለተግባር ፈተና ብቻ) | 600 |
| 34 | ማሰልጠኛ ተቋማት ሰልጣኞቻቸውን ለፈተና ሲያቀርቡ የዳግም ፈተና ጨምሮ ለአንድ ጊዜ ለአንድ ሰልጣኝ የኮቲ የሚከፈል (በማሰልጠኛ ተቋማት የሚከፈል) | 150 |
| 35 | ከፍርድ ቤት፣ ፍትህ እና ፖሊስ ተቋማት ውጭ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ትክክለኛነት በደብዳቤ ማረጋገጥ | 500 |
| 36 | የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋጫ ማገድና እገዳ ማንሳት (እገዳው ሲነሳ የሚከፈል) | 1000 |
| 37 | ለሹፌር ቅጥር የምዘና አገልግሎት ሲሰጥ (ለአንድ ዙር ለሁሉም ተፈታኝ) | 2000 |
| 38 | በመንጃ ፈቃድ ላይ የስምና የልደት ቀን ለውጥ | 1500 |

## 5. የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 1 | ያለፈቃድ የአካል ለውጥ ያደረገ ተሽከርካሪ (ትክክል ሆኖ ከተገኘ) | 5000 |
| 2 | ያለፈቃድ የሞተር ለውጥ ያደረገ ተሽከርካሪ (ትክክል ሆኖ ከተገኘ) | 5000 |
| 3 | ያለፈቃድ የሻንሲ ለውጥ ያደረገ ተሽከርካሪ (ትክክል ሆኖ ከተገኘ) | 5000 |
| 4 | ያለፈቃድ የሞተር ቁጥር ማስመታት | 5000 |
| 5 | ያለፈቃድ የሻንሲ ቁጥር ማስመታት | 5000 |
| 6 | የተለያዩ ስሌዳወች ታሪፍ | |
| 6.1 | ተላላፊ ሰሌዳለ መስጠት ለ3 ቀን | 500 |
| 6.1.1 | ለተላላፊ ሰሌዳ ማራዘሚያ (ድጋሚ) ለ 3 ቀን | 700 |
| 6.1.2 | ለተላላፊ ሰሌዳ ቅጣት በቀን | 500 |
| 6.2 | የእለት ሰሌዳ | |
| 6.2.1 | የእለት ሰሌዳ ሲሰጥ (ለ30 ቀን) | 2000 |
| 6.2.2 | ከ30 ቀን በኂላ በቀን የሚከፈል ቅጣት | 200 |
| 6.2.3 | ለተሽከርካሪ አስመጭዎች የተላላፊ ሰሌዳ መስጠት | 5000 |
| 6.3 | መደበኛ (ቋሚ) ሰሌዳ በነጠላ | |
| 6.3.1 | 460 x110 ሚ.ሜ (ሬክታንግል) | 1900 |
| 6.3.2 | 280x200 ሚ.ሜ (አራት ማዕዘን) | 2200 |
| 6.3.3 | 340 x200 ሚ.ሜ (አራት ማዕዘን ተሳቢ) | 2350 |
| 6.3.4 | 305 x200 ሚ.ሜ (ልዩ አራት ማዕዘን ለቤት) | 2650 |
| 6.3.5 | 520x110 ሚ.ሜ (ሬክታንግል) | 2200 |
| 6.3.6 | 240x130 ሚ.ሜ (ሞተር ሳይክል) | 1500 |
| 7 | የቴምብር ቀረጥ 2 ከመቶ (የተሽከርካሪ የባለቤትነት ማስመዝገቢያ) በአዋጅ ቁጥር 110/1990 የፀደቀ በመሆኑ በነበረው መቶኛ የሚቀጥል ነው። | |
| 8 | ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ እና የምዝገባ ተለጣፊ ምልክት ( ቦሎ) ሲሰጥ | |
| 8.1 | ለሞተር ሳይክል | 250 |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 8.2 | ለግል አውቶሞቢሎች ለባለ ሶስት እግር እና ለህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የነዳጁን መቀመጫ ጨምሮ | |
| 8.2.1 | ከአምስት የማይበልጥ መቀመጫ ላላቸው ለግል አውቶሞቢሎችና ባለ 3 እግር ላላቸው ሞተር ሳይክሎች | 500 |
| 8.2.1.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ መቀመጫ | 7 |
| 8.2.2 | ከ 6 እስከ 44 መቀመጫ ላላቸው | 650 |
| 8.2.2.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ መቀመጫ | 7 |
| 8.2.3 | ከ45 እስከ 64 መቀመጫ ላላቸው | 650 |
| 8.2.3.1 | በተጨማሪ መቀመጫ | 7 |
| 8.2.4 | 65 መቀመጫ እና በላይ ላላቸው | 700 |
| 8.2.4.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ መቀመጫ | 7 |
| 8.3 | የሚከተለውን የኩንታል ጭነት መጠን ላላቸው ተሽከርካሪወች | |
| 8.3.1 | ከ5 እስከ 70 ኩንታል ለሚጭኑ | 650 |
| 8.3.1.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ኩንታል | 7 |
| 8.3.2 | ከ71 ኩንታል እስከ 120 ኩንታል | 750 |
| 8.3.2.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ኩንታል | 6 |
| 8.3.3 | ከ120 ኩንታል በላይ ለሚጭኑ | 4000 |
| 8.3.3.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ኩንታል | 5 |
| 8.3.4 | ማንኛውም ተሳቢ | 4000 |
| 8.3.4.1 | በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ኩንታል | 4 |
| 8.4 | ለልዩ ተንቀሳቃሽ መሳሪያ {ተሽከርካሪ) | 750 |
| 9 | ለዓመታዊ ምርመራ ተለጣፊ ምልክት (ቦሎ) ግልባጭ መስጠት | |
| 9.1 | የዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ተለጣፊ ምልክት ስህተት ሲኖረው (በ 10 ቀን ውስጥ ቀርቦ ካላስተካከ ) | መጀመሪያ ቦሎ ሲወስድ የከፈለውን ክፍያ ይከፍላል |
| 9.2 | የዓመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ተለጣፊ ምልክት ብልሽት ወይም መጥፋት ሲያጋጥም ምትክ ለመስጠት | መጀመሪያ ቦሎ ሲወስድ የከፈለውን ክፍያ ይከፍላል |
| 9.3 | የአመታዊ ተለጣፊ ምልክት ቅጣት ቦሎ መደረግ ከነበረበት ቀን በየአንዳንዱ 15 ቀን | 100 |
| 10 | የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ | 300 |
| 11 | የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ ሊብሬ መስጠት | 1000 |
| 12 | ሊብሬ ሲበላሽ፣ ወይንም ሲጠፋ ምትክ መስጠት | 1000 |
| 13 | የተሽከርካሪ ስሌዳ እና አገልግሎት ለውጥ ምዝገባ | 15000 |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 14 | የተሽከርካሪ የአካል ለውጥ ፈቃድ አገልግሎት | 1000 |
| 15 | የተሽከርካሪ የአካል እና የአገልግሎት ለውጥ ምዝገባ አገልግሎት | 5000 |
| 16 | የሻንሲ እና የሞተር ለውጥ ፈቃድ አገልግሎት | 500 |
| 17 | የሻንሲ ለውጥ ምዝገባ አገልግሎት | 400 |
| 18 | የሻንሲ ቁጥር ምዝገባ አገልግሎት | 500 |
| 19 | የሞተር ለውጥ ምዝገባ አገልግሎት | 400 |
| 20 | የሞተር ቁጥር ምዝገባ አገልግሎት | 500 |
| 21 | የሻንሲ ቁጥር እና የሞተር ቁጥር ማስመቻ ፈቃድ አገልግሎት | 500 |
| 22 | የተሽከርካሪ የእዳ እና እገዳ ምዝገባ አገልግሎት(ከፖሊስና ከፍትህ ለሚፃፍ ደብዳቤ በነፃ) ሆኖ | 300 |
| 23 | የተሽከርካሪ የእዳ እና እገዳ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ለአበዳሪ ተቋማት (ለባኮችና ለማይክሮ ፋይናስ ተቋማት) ሲሆን የብድሩን 1% (አንድ ፐርሰንት) ይከፈላል | |
| 24 | የነዳጅ አጠቃቀም ልኬታ ኖርማላይዜሽን ባለስልጣኑ ላይ በዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ የሚሰበሰብ | 1000 |
| 25 | የተሽርካሪ ሽያጭ ውል ማፍረስ (ያፈረሰው አካል ይከፍላል) | 1000 |
| 26 | የተሽከርካሪ የባለቤትነት የስም ዝውውር አገልግሎት | 2000 |
| 27 | የተሽከርካሪ ፋይል ከአማራ ክልል ወደ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ማዛወር | 500 |
| 28 | በክልሉ ውስጥ ከዞን ዞን የሚደረግ የተሽከርካሪ የፋይል ዝውውር መላክም ሆነ መቀበል | 500 |
| 29 | ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወደ አማራ ክልል የሚመጡ የተሽከርካሪ የፋይል ዝውውር አገልግሎት | 1000 |
| 30 | ከመንግስታዊ ተቋማት ውጭ በፅሁፍ መረጃ መስጠት | 500 |
| 31 | የተሽከርካሪ ሊብሬ እና ሰሌዳ በአደራ ማስቀመጥ አገልግሎት (ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ) | 1000 |
| 32 | የተሽከርካሪ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት | 100 |
| 33 | ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚፃፍ ደብዳቤ ከቀረጥ ነፃ ለገባ ተሽ/ሪ ቀረጥ ማንሳት አገልግሎት | 1000 |
| 34 | ለጠፋ ቦሎ፣ ለጠፋ ሊብሬ፣ ለጠፋ ሰሌዳ እንዲሁም ሌሎች ማሳወቂያ ለፖሊስ ወይም ለፕረስ ለሚሰጥ መረጃ ( በእያዳንዱ የሚከፈል ) | 500 |
| 35 | አዲስ የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ መስጠት | 8000 |
| 36 | አዲስ የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ ማደስ | 6000 |
| 37 | ያገለገለ የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ መስጠት | 7000 |
| 38 | ያገለገለ የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ ማደስ | 5000 |
| 39 | የተሽከርካሪ አስመጭነት ፈቃድ ሲበላሽና ሲጠፋ ትክ መስጠት(ለሁሉም) | 1500 |
| 40 | የተሽከርካረሪ አስመጭነት የአድራሻ ለውጥ | 2500 |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 41 | የፍጥነት መገደቢያ አዲስ ፈቃድ መስጠት | 4000 |
| 42 | የፍጥነት መገደቢያ ፈቃድ ማደስ | 3000 |
| 43 | ቴምብር ቁርጥ | |
| 43.1 | የሻንሲ ለዉጥ 2 መቶኛ ክፍያ (2%) | |
| 43.2 | የሞተር ለዉጥ 2 መቶኛ ክፍያ (2%) | |
| 43.3 | የአካል ለዉጥ 2 መቶኛ ክፍያ (2%) | |
| 43.4 | የተሽከርካሪ ጨረታ ሽያጭ 2 መቶኛ ክፍያ (2%) | |
| 44 | አዲስ ተሽከርካሪ ለማስመዝገብ 2 መቶኛ ክፍያ (2%) | |
| 45 | የተሽከርካሪ ዋጋ መገመቻ አገልግሎት | |
| 45.1 | ለሞተር ብስክሌት | 300 |
| 45.2 | እስከ አምስት መቀመጫ አውቶሞቢልና ሦስት እግር ሞተር ሣይክል | 500 |
| 45.3 | ከ6-17 መቀመጫና ከ1-15 ኩንታል | 700 |
| 45.4 | ከ18-44 መቀመጫና ከ16-49 ኩንታል | 800 |
| 45.5 | ከ45 መቀመጫ በላይና ከ50-100 ኩንታል | 900 |
| 45.6 | ከ100 ኩንታል በላይ | 1000 |
| 45.7 | ለልዩ ተንቀሳቃሽ | 500 |
| 46 | የጀልባ ፈቃድ መስጠት | |
| 46.1 | ከ1 እሰከ 12 ሰው የመጫን አቅም | 700 |
| 46.2 | ከ13 እሰከ 24 ሰው የመጫን አቅም | 900 |
| 46.3 | ከ25 እሰከ 36 ሰው የመጫን አቅም | 1100 |
| 46.4 | ከ37 እሰከ 48 ሰው የመጫን አቅም | 1300 |
| 46.5 | ከ49 ሰው በላይ የመጫን አቅም | 1500 |
| 47 | የጀልባ ፈቃድ እድሳት | |
| 47.1 | ከ1 እሰከ 12 ሰው የመጫን አቅም | 500 |
| 47.2 | ከ13 እሰከ 24 ሰው የመጫን አቅም | 700 |
| 41.3 | ከ25 እሰከ 36 ሰው የመጫን አቅም | 900 |
| 47.4 | ከ37 እሰከ 48 ሰው የመጫን አቅም | 1100 |
| 47.5 | ከ49 ሰው በላይ የመጫን አቅም | 1300 |
| 47.6 | በወቀቱ ያላሳደሰ እስከ አንድ ዓመት ድረስ በየወሩ ቅጣት | 200 |
| 47.7 | ሳያሳድስ አንድ አመት ያለው ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ መቀጠል ከፈለገ በአዲስ ፈቃድ ማውጣት ይችላል፡፡ | |
| 48 | ለጥገና ተቋም (ለጋራጅ) ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ፈቃድ መስጠት | |
| 48.1 | ለደረጃ 4 | 4000 |
| 48.2 | ለደረጃ 3 | 3500 |
| 48.3 | ለደረጃ 2 | 3000 |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 48.4 | ለደረጃ 1ና ደረጃ ላልወጣላቸው | 2500 |
| 49 | ለጥገና ተቋም (ለጋራጅ) ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ፈቃድ ማደስ | |
| 49.1 | ለደረጃ 4 | 3500 |
| 49.2 | ለደረጃ 3 | 3000 |
| 49.3 | ለደረጃ 2 | 2500 |
| 49.4 | ለደረጃ 1ና ደረጃ ላልወጣላቸው | 2000 |
| 50 | የጥገና ተቋም አድራሻ ለውጥ በፈቃደ | 2000 |
| 51 | ለጥገና ተቋም ለጠፋ ወይም ለተበላሸ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ትክ መስጠት | |
| 51.1 | ለመጀመሪያ ጊዜ | 500 |
| 51.2 | ለሁለተኛ ጊዜ | 700 |
| 52 | የጥገና ተቋም የእድሳት ጊዜ ሲያልፍ | |
| 52.1 | እስከ አንድ ወር | 100 |
| 52.2 | ከአንድ ወር በኂላ እስከ 3 ወር | 300 |
| 52.3 | ከ3 ወር በኂላ ከተራ ቁጥር 52.2 ላይ እየተደመረ በየወሩ የሚከፈል ቅጣት | 1000 |
| 53 | የተሽከርካሪ የአካል ለውጥና ጥገና ጋራዥ ፈቃድ መስጠት | |
| 53.1 | ለደረጃ 1 | 3000 |
| 53.2 | ለደረጃ 2 | 4000 |
| 53.3 | ለደረጃ 3 | 5000 |
| 53.4 | ለደረጃ 4 | 6000 |
| 54 | የተሽከርካሪየአካል ለውጥና ጥገና ጋራዥ ፈቃድ ማደስ | |
| 54.1 | ለደረጃ 1 | 2000 |
| 54.2 | ለደረጃ 2 | 3000 |
| 54.3 | ለደረጃ 3 | 4000 |
| 54.4 | ለደረጃ 4 | 5000 |
| 55 | የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት ለሁሉም ደረጃዎች | 8000 |
| 56 | የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፈቃድ እድሳት | 5000 |
| 57 | ለሁሉም ደረጃ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ፈቃድ እድሳት ቅጣት ከማሳደሻ በተጨማሪ ለዘገየበት ለ15 ቀን | 200 |
| 58 | ለጠፋ ወይም ለተበላሸ የምርመራ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ትክ መስጠት | |
| 58.1 | ለመጀመሪያ ጊዜ | 400 |
| 58.2 | ለሁለተኛ ጊዜ | 1000 |
| 59 | የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም የአድራሻ ለውጥ | 3500 |

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 60 | የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም ቅርንጫፍ መክፈት | 5000 |

## 6. የትራንስፖርት አገልግሎት ኢንስፔክሽን የአገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነቶች | ቀላል ችግር በ7 ቀን እና ከባድ ችግ በ10 ቀን ተስተካክሎ ከቀረበ | ለማስተካከል ከተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ እስከ 15 ቀን አሳልፎ አስተካክሎ ከቀረበ | ለማስተካከል ከተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ከ15 ቀን በላይ አሳልፎ አስተካክል ከቀረበ |
|---|---|---|---|---|
| | ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ | | | |
| 1 | ለባለሁለት እና ሦሥት እግር ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 400.00 | ብር 600.00 | ብር 800.00 |
| 2 | እስከ 11 ሰው መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 600.00 | ብር 800.00 | ብር 1000.00 |
| 3 | ከ12 እስከ 44 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 800.00 | ብር 1000.00 | ብር 1200.00 |
| 4 | 45 ሰውና በላይ መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 1000.00 | ብር 1200.00 | ብር 1500.00 |
| 5 | እስከ 35 ኩንታል የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 800.00 | ብር 1000.00 | ብር 1200.00 |
| 6 | ከ36 እስከ 70 ኩንታል የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 1000.00 | ብር 1200.00 | ብር 2000.00 |
| 7 | ከ71 እስከ 150 ኩንታል የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 1000.00 | ብር 2500.00 | ብር 3500.00 |
| 8 | ከ150 ኩንታል በላይ የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 1500.00 | ብር 3000.00 | ብር 4000.00 |
| 9 | እስከ 18000 ሊትር ፈሳሽ የሚጭን ተሽከርካሪ ምርመራ፣ | ብር 1000.00 | ብር 2500.00 | ብር 3500.00 |

## 7. የትራንስፖርት አገልግሎት ስምሪት የአገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የሚሰጠዉ የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 1 | ለአዲስ የህዝብ ማመላለሻ የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ | 1000 |
| 2 | የህዝብ ማመላለሻ ኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት፣ | 1000 |
| 3 | የህዝብ ማመላለሻ ኦፕሬተር ፈቃድ እድሳት ጊዜው ሲያልፍ ቅጣት በየወሩ | 500 |
| 4 | የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራትና ድርጅቶች | |
| 4.1 | ለአዲስ የህዝብ ትራንስፖርት ማህበራት(ድርጅ) ፈቃድ መስጠት | |
| 4.1.1 | የአባላት ብዛት 50 ከሆነ | 500 |
| 4.1.2 | የአባላት ብዛት ከ51- 100 ከሆነ | 1500 |
| 4.1.3 | የአባላት ብዛት ከ101 በላይ ከሆነ | 2500 |
| 4.2 | የነባር የህዝብ የትራንስፖርት ማህበራት /ድርጅት/ ፈቃድ እድሳት | |
| 4.2.1 | የአባላት ብዛት 50 ከሆነ | 500 |
| 4.2.2 | የአባላት ብዛት ከ51- 100 ከሆነ | 15000 |
| 4.2.3 | የአባላት ብዛት ከ101 በላይ ከሆነ | 2500 |
| 4.4 | የከተማ ትራንስፖርት ማህበራት/ድርጅት/ | |
| 4.4.1 | የባጃጅ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር /ድርጅት/ ፈቃድ ሲሰጥ | |
| 4.4.1.1 | የአባላት ብዛት እስከ 50 | 500 |
| 4.4.1.2 | የአባላት ብዛት ከ51-100 | 1000 |
| 4.4.1.3 | የአባላት ብዛት ከ101-200 | 1500 |
| 4.4.1.4 | የአባላት ብዛት ከ201-300 | 2000 |
| 4.4.1.5 | የአባላት ብዛት ከ 301-400 | 2500 |
| 4.5 | የባጃጅ ታክሲ ባለንብረቶች ማህበር /ድርጅት/ ፈቃድ እድሳት | |
| 4.5.1 | የአባላት ብዛት እስከ 50 | 500 |

| ተ.ቁ | የሚሰጠዉ የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 4.5.2 | የአባላት ብዛት ከ51-100 | 1000 |
| 4.5.3 | የአባላት ብዛት ከ101-200 | 1500 |
| 4.5.4 | የአባላት ብዛት ከ 201-300 | 2000 |
| 4.4.5 | የአባላት ብዛት ከ 301-400 | 2500 |
| 4.5 | ሚኒባስ /ሚዲባስ እና የኤርፖርት ታክሲ ማህበር/ድርጅት/ ፈቃድ ሲሰጥ | |
| 4.5.1 | የአባላት ብዛት እስከ 50 | 500 |
| 4.5.2 | የአባላት ብዛት ከ51-100 | 1000 |
| 4.5.3 | የአባላት ብዛት ከ101-200 | 1500 |
| 4.5.4 | የአባላት ብዛት ከ201-300 | 2000 |
| 4.5.5 | የአባላት ብዛት ከ 301-350 | 2500 |
| 4.6 | ሚኒባስ /ሚዲባስ እና የኤርፖርት ታክሲ ማህበር /ድርጅት/ ፈቃድ እድሳት | |
| 4.6.1 | የአባላት ብዛት እስከ 50 | 500 |
| 4.7.2 | የአባላት ብዛት ከ51-100 | 1000 |
| 4.6.3 | የአባላት ብዛት ከ101-200 | 1500 |
| 4.64 | የአባላት ብዛት ከ201-300 | 2000 |
| 4.6.5 | የአባላት ብዛት ከ 301-350 | 2500 |
| 4.7 | የታክሲ ማህበራት/ድርጅት/ ፈቃድ ሲጠፋ ትክ | 500 |
| 4.8 | የታክሲ ማህበራት ፈቃድ /ድርጅት/ ሲበላሽ ትክ | 300 |
| 4.1 | የሜትር ታክሲ ማህበራት/ድርጅት/ አዲስ ፈቃድ መስጠት | 3000 |
| 4.11 | የሜትር ታክሲ ማህበራት /ድርጅት/ ፈቃድ እድሳት | 2000 |
| 4.12 | የሜትር ታክሲ ማህበራት /ድርጅት/ ፈቃድ ሲጠፋ ትክ | 1000 |
| 4.13 | የሜትር ታክሲ ማህበራት /ድርጅት/ ፈቃድ ሲበላሽ ትክ | 500 |
| 4.14 | የጭነት ትራንስፖርት ማህበራት | |

| ተ.ቁ | የሚሰጠዉ የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 4.14.1 | ለአዲስ የጭነት የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ መስጠት | |
| 4.14.1.1 | የአባላት ብዛት እስከ 50 ከሆነ | 1000 |
| 4.14.1.2 | የአባላት ብዛት ከ51 እስከ 100 ከሆነ | 1500 |
| 4.14.1.3 | የአባላት ብዛት 101 እስከ 150 ከሆነ | 2000 |
| 4.14.1.4 | የአባላት ብዛት 151 እስከ 200 ከሆነ | 2500 |
| 1.15 | የነባር የጭነት የትራንስፖርት ማህበራት ፈቃድ እድሳት | |
| 4.15.1 | የአባላት ብዛት እስከ 50 ከሆነ | 1000 |
| 4.15.2 | የአባላት ብዛት ከ51 እስከ 100 ከሆነ | 1500 |
| 4.15.3 | የአባላት ብዛት 101 እስከ 150 ከሆነ | 2000 |
| 4.15.4 | የአባላት ብዛት 151 እስከ 200 ከሆነ | 2500 |
| 4.16 | የጭነት ማህበር ፈቃድ ሲጠፋ ትክ | 1000 |
| 4.17 | የጭነት ማህበራት ፈቃድ ሲበላሽ ትክ | 500 |
| 4.18 | የጭነት የትራንስፖርት ድርጅቶች | |
| 4.18.1 | ለግለሰብ የጭነት ተሽከርካሪ ባለንብረቶች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት | 1000 |
| 4.18.2 | ለግለሰብ የጭነት ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት ለማድረግ | 1000 |
| 4.19 | የትራንስፖርት ድርጅቶች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስጠት | |
| 4.19.1 | እስከ 50 ተሽከርካሪ ያለዉ የትራንስፖርት ድርጅት ብር | 2000 |
| 4.19.2 | ከ51-100 ተሽከርካሪ ያለዉ የትራንስፖርት ድርጅት | 2500 |
| 4.19.3 | ከ100 ተሽከርካሪ በላይ ያለዉ የትራንስፖርት ድርጅት | 3000 |
| 4.2 | የትራንስፖርት ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ እድሳት | |
| 4.20.1 | እስከ 50 ተሽከርካሪ ያለዉ | 2000 |
| 4.20.2 | ከ51-100 ተሽከርካሪ ያለዉ የትራንስፖርት ድርጅት | 2500 |
| 4.20.3 | ከ100 ተሽከርካሪ በላይ ያለዉ የትራንስፖርት ድርጅት | 3000 |

| ተ.ቁ | የሚሰጠዉ የአገልግሎት አይነት | አዲሱ የአገልግሎት ክፍያ |
|---|---|---|
| 4.21 | አዲስ ህዝብ ተሽከርካሪ ባለንብረት የማህበር አባል ማድረግ | 300 |
| 4.23 | አዲስ የከተማ ታክሲ ተሽከርካሪዎች ባለንብረት የማህበር አባል ማድረግ | 200 |
| 4.24 | አዲስ የጭነት ተሽከርካሪ ባለንብረቶች የማህበር አባል ማድረግ | 500 |
| 4.25 | የስምሪት መልቀቂያ መስጠት | 150 |
| 4.26 | የልዩ ጉዙ ፈቃድ መስጠት | 200 |
| 4.27 | ሁሉም ማህበር /ድርጅት/ በወቅቱ ፈቃዱን ካላሳደሰ ቅጣት | |
| 4.27.1 | እስከ አንድ ወር ብር | 300 |
| 4.27.2 | ከአንድ ወር በኂላ እስከ 3 ወር ብር | 500 |
| 4.27.3 | ከ3 ወር በኂላ እስከ 5 ወር ብር | 1000 |
| 4.27.4 | ከ5 ወር በኂላ ከተራ ቁጥር 4.27.3 ላይ በየወሩ | 300 |
| 4.28 | የልዩ ተሽከርካሪዎች /የተሽከርካሪ ማንሻና ማዘያ ፈቃድ መስጠት | 3000 |
| 4.29 | የልዩ ተሽከርካሪ ዎች /የተሽከርካሪ ማንሻና ማዘያ ፈቃድ እድሳት | 1500 |
| 4.30 | የልዩ ተሽከርካሪ ዎች /የተሽከርካሪ ማንሻና ማዘያ ፈቃድ ሲጠፋ ትክ መስጠት | 1500 |
| 4.31 | የልዩ ተሽከርካሪ ዎች /የተሽከርካሪ ማንሻና ማዘያ ፈቃድ ሲበላሽ ትክ መስጠት | 1000 |
| 4.32 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / የኦፐሬተር ፈቃድ መስጠት | 3000 |
| 4.33 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / የኦፐሬተር ፈቃድ እድሳት | 2000 |
| 4.34 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / የኦፐሬተር ፈቃድ ሲጠፋ ትክ መስጠት | 500 |
| 4.35 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / የኦፐሬተር ፈቃድ ሲበላሽ ትክ መስጠት | 300 |
| 4.36 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / ብቃት መረጋገጫ ፈቃድ መስጠት | 500 |
| 4.37 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እድሳት | 300 |
| 4.38 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድሲጠፋ ትክ መስጠት | 500 |
| 4.39 | ኮድ 3 የኪራይ አዉቶሞቢል / የኪራይ ተሽከርካሪ / ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲበላሽ ትክ መስጠት | 300 |
| 4.40 | የሞተር ሳይክል የኦፐሬተር ፈቃድ አገልግሎት | 100 |
| 4.41 | የሞተር ሳይክል መታወቂያ መስጠት | 100 |
| 4.42 | የሞተር ሳይክል መታወቂያ እድሳት | 50 |

# ክፍል ሦሥት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛዉም የሚመለከተው አካል ይህን መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

9. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

10. **መመሪያዉን ስለመማሻሻል**

ይህን መመሪያ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛዉም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

11. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

1/ ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን ዋና ዳሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ከመስከረም 28/2016 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

**ዘውዱ ማለደ በላይ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**

**ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ ባለስልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**